## ከክልል ውጪ ትምህርት የመከታተል ፖሊስ ምንድን ነው?

ከመዋዕለ ሕጻናት –12 (K-12 ) ከክልል ውጪ የሆኑ **ከ 10 ጊዜ በላይ ሳያስፈቅዱ ወይንም 20 ጊዜ ያለ አጥጋቢ ምክንያት የዘገዩ** ተማሪዎች በትምህርት ዓመቱ ማብቂያ ላይ ወደ ክልል ትምህርት ቤቶታቸው እንዲመለሱ የሚጠየቁ ሲሆን ይህም ሊሆን የሚችለው ከመኖሪያ አጎራባች ክልል ውጪ የሆንው ትምህርት ቤት የዲሲፒኤስን ትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት መደረግ የሚገባውን አስፈላጊ የድጋፍ እርምት እርምጃዎች (interventions) ሁሉ ሥራ ላይ ያዋለ እና የመዘገበ ሆኖ ሲገኝ ነው። ፖሊሲው ለቅድመ ትምህርት (preschool) ወይም ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (Pre-Kindergarten) ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ተግባር ላይ የሚውል አይደለም።

## ትምህርት ገበታ ላይ ለመግኘት ከተማሪዎች ሁሉ የሚጠበቅባቸው ምንድን ነው?

- በየዕለቱ ከትምህርት ቤት እና ከትምህርት ክፍል **በሰዓቱ መድረስ።**
- **የመማሪያ መጻሕፍትን** እና የትምህርት ቁሳቁሶችን ይዞ ከክፍል መገኘት።
- ለበለጠ ሥራ ወይንም መሟላት ለሚገባው ተስጥተው ለነበሩ ሥራዎች (assignments) ምን ምን እንደነበሩ **መምህሩን መጥጠየቅ**
- ላመለጡ የትምህርት ቀናት ለክልሉ ትምህርት ቤት **ማስረጃዎችን ማቅረብ።**
- አካዳሚክ ነክ ወይንም ሌሎች አሳሳቢ ጉዳዮች (ለምሳሌ የደህነት ዋስትና ወይንም የመጓጓዣ ችግር) የመሳሰሉ



## ቋሚ ቤት ከሌለኝ እና ድጋፍ የሚያስፈልገኝ ከሆነ ምንድን ነው ማድረግ ያለብኝ?

የዲሲፒኤስ ለቤት የለሽ ልጆች እና ለወጣቶች ፕሮግራም (The DCPS Homeless Children and Youth Program [HCYP]) በጊዜያዊ ወይንም በሽግግር ቤት ውስጥ ለሚኖሩ ተማሪዎች የሚከተሉትን ድጋፎች ይሰጣል፤

- በትምህርት ቤት ምዝገባ፣
- የመጓጓዣ አገልግሎት፣
- በግል ለሚያስፈልጉ ነገሮች (የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ፣ የትምህርት ቁሳቁሶች እና ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች)።

ለበለጠ መረጃ እባክዎን በትምህርት ቤትዎ የቤት የለሽ ልጆች መብት ተጠሪ የሆነውን ሰው ወይንም የዲሲፒኤስ DCPS HCYP Specialist ን በ (202)-576-9502 ደውለው ያነጋግሩ።



## የበለጠ መረጃ ለማግኘት ማንን ነው የማነጋግረው?


District of Columbia Public Schools
Office of Youth Engagement
Student Attendance & Support Service
1200 First Street, NE
Washington, DC 20002
ስልክ 202-442-4404
ፋክስ 202-535-1338


DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# ዛሬ ትምህርትህን ተከታተል

# ነገ ደግሞ ውጤት አምጣ




ዲሲፒኤስ ትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት ጽሑፍ (AMHARIC)
ነሀሴ (August) 2014 በድጋሜ ተጣርቶ የቀረበ

## የመጀመሪያው ቀን፣ ሁሉ ቀን

በዲሲፒኤስ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) እያንዳንዱ ተማሪ፣ **በየዕለቱ ና በሰዓቱ** ትምህርት ቤት በመገኘት የአካዳሚክ ትምህርቱን ማሳካቱን ዕውን ማድረጉን ማረጋገጥ ግባችን ነው። በየዕለቱ ከትምህርት ገበታ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ብዙ ትምህርት የሚቀስሙና ትምህርታቸውም የተዋጣለት ነው’።

ዲሲፒኤስ፣ ከቀሪነት ሁሉ ያለፈቃድ መቅረትን ብቻ ከመቆጣጠር ወደ **ዘወትር ትምህርት ገበታ ላይ በሚገኙ** (In-Seat Attendance [ISA]) ላይ ክትትል በማድረግ የትኩረት ለውጥ አድር ጓል። አንዳንድ ጊዜ ከትምህርት ገበታ የመቅረት ሁኔታዎች ሊወገዱ የማይችሉ ቢሆንም ልጆች **በፈቃድም ይሁን ያለፈቃድ በመቅረት** በርካታ ትምህርቶች ሲያመልጧቸው እና - በትምህርታቸው ወደ ኋላ ይቀራሉ።

**ከትምህርት ገበታ የተቀረበት ቀን ፣ ለመማር ያመለጠ እድል ነው።** ዘወትር ከትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን ከማናቸውም ጉዳይ ሁሉ ቅድሚያ እንስጠው !

## ትምህርት ቤት ገብቶ ትምህርት መካታተል አስፈላጊ ነው ?

**እዎን፣ ትምህርት ቤት ገብቶ ትምህርት መከታተል በህግ የሚያስጠይቅ አስፈላጊ ጉዳይ ነው**! በተያዘው ዓመት በመስከረም (September) 30th ላይ አምስት ዓመት የሚሞላቸው ወይንም ከዚህ በፊት ቀደም ብሎ ተማሪዎች ሁሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምረቃ የሚጠይቅውን እስኪያሟሉ ወይንም 18ተኛ ዓመት የልደት በዓላቸው ላይ እስከ ሚደርሱ ድረስ በየዐለቱ ትምህርት ገበታ እየተገኙ ትምህርት መከታተል አለባቸው።

## ማጋጣነት (Truancy) ምንድን ነው ?

ማጋጣነት፣ ታዳጊ የሆኑ ልጆች (5-17 ዓመት እድሜ ለሞላቸው) ተቀባይነት ባለውም ሆነ በሌለው፣ ወላጅ ዕውቆም ሆነ ሳያውቅ፣ በም ከንያትም

## ተቀባይነት ያለው መቅረት ምን ዐይነት ነው?

<u>**ተቀባይነት ያለው መቅረት** (Excused absences)</u> እድሜ ያቸው ለትምህርት የድረሱ ተማሪዎች ተቀባይነት ባለው አሳማኝ ሁኔታ እና በወላጅ በሚደገፍ ምክንያት ከትምህርት ቤት ሲቀሩ ነው። <u>ተቀባይነት ወይንም አሳማኝነት ያለው ምክንያት የሚከተሉትን ያከትታል፤</u>

- የተማሪ ሕመም (ተማሪው ከ 5 ቀናት በላይ ከቀረ የሀኪም ወረቀት ያስፈልገዋል)፣
- በተማሪው የቅርብ ቤተሰብ ሞት ምክንያት፣
- የፍርድ ቤት ችሎት ላይ ተማሪው ከሻሽ፣ ተከሳሽ፣ ተወካይ፣ እማኝ፣ ወይም የሸንጎ አባል ሆኖ መመደብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤
- የሀይማኖታዊ እምነት በዓልን ለማክበር፤
- በአየር ንብረት መዛባት ምክንያት፣ በትምህርት ቤት የደህንነት ዋስትና መደፍረስ ወይንም በጊዜያዊ ደራሽ ምክንያቶች የተነሣ የትምህርት ቤት መዘጋት፤
- በህመም ምክንያት እንደ የህክምና የሀኪም ቀጠሮ በመሳሰሉ ምክንያት (የሀኪም ወረቀት ያስፈልጋል፤)
- መጓጓዣ እንዲቀርብ ህግ በሚያዝበት ሁኔታ፣ ዲሲ መጓጓዣ ማቅረብ አለመቻል፤
- በውትድርና ተግባር ላይ የተሰማራ ወላጅን ለመጎብኘት፤
- ዲሲፒኤስ አጽድቆ በተቀበለው ሁኔታ ምክንያት፤

<u>**ያለ አጥጋቢ ምክንያት መቅረት፤**</u> እድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ ተማሪዎች ያለ በቂ አጥጋቢ ምክንያት፣ በውላጅ ፈቃድም ይሁን ያለወላጅ ፈቃድ ከትምህርት ቤት ሳይገኙ ሲቀሩ ነው። <u>ያለ አጥጋቢ ምክንያት ከትምህርት ገበታ መቅረት የሚከተሉትን ምሳሌዎች የመሳሰሉ ያካትታል፤</u>

- የቤተሰብ የዕረፍት ሽርሽር
- ሕጻን ልጅ መጠበቅ
- መገበያየት (Shopping)
- መላላክ
- ጠዋት ከእንቅልፍ እያረፈዱ መነሣት (Oversleeping)
- ክፍል እየጣሉ መሄድ
- ሥራ ፍለጋ
- የቤተሰብ የዕርፍት በዓል
- የወላጅ ህመም

**ከቀኑ ትምህርት ከመቶ 20% (እጅ) የሚሆነውን ያህል ጊዜ ከትምህርት ገበታ ላይ የማይገኙ ተማሪዎች ለዚያ ዕለት በሙሉ ያለ አጥጋቢ ምክንያት የቀሩ ተብሎ ይያዝባቸዋል።**

## አንድ ተማሪ ያለ በቂ ምክንያት ከክፍል ሲቀር ምን ይድረጋል?

**1&2** — መምህር ወደ ተማሪው ቤት ስልክ ይደውላል

**3** — የማሳሰቢያ ደብዳቤ ወደ ተማሪው ቤት እንዲላክ ይደረጋል

**5** — *ማሳሰቢያ ደብዳቤ ወደ ተማሪው ቤት ይላካል
ተማሪ ድጋፍ ቡድን ስብሰባ ላይ (SST) ወላጅ መገኘት አለበት
*ወላጅ ስብሰባ ላይ ካልተገኘ (SST) የቤት ጉብኝት ይካሄዳል

**7** — ሜትሮ ፖሊታን ፖሊስ መምሪያ (MPD) ማስጠ ንቀቂያ ደብዳቤ ወደ ተማሪው ቤት ይላካል

**10** — **5-13 እድሜ፤** ለትምህርት ዋጋ ባለምስጠት ምክንያት ወላጆችና ቤተሰብ አገልግሎት ይመራል
**14 እና በላይ እድሜ፤** ወላጅ የ SST ክትትል ስብሰባ ላይ መገኘት አለበት ስብሰባ ላይ መገኘት ይዋርበታል

**15** — * ማሳሰቢያ ደብዳቤ ወደ ተማሪው ቤት ይላካል
**ከ 5-17 እድሜ፤** ወደ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት ወይም ማኅበራዊ ጉዳይ አገልግሎት ጽሕፈት ቤት እንዲመራ ይደረጋል

**ዲሲፒኤስ ትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት ጽሑፍ (AMHARIC)**
**ነሀሴ (August) 2014 በድጋሜ ተጣርቶ የቀረበ**